ፓኖራማ ቁጥር 67

የትዝብት ድማስ

ሚያዝያ 11 ቀን 2001 ዓም

## አማራጭ መች ጠፍቶ

በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ለሚኖር ማነኛውም ኅብረተስብ ሕይወቱን ለመምራት የሚያ ስችለውን ሥርዓተ-መንግሥት ለመመስረት፥ የተለያዩ አማራጮችን መፈለግ፥ ማፈላለግ፥ መመርመርና ማስተናገድ ግድ ይለዋል፡፡ያ ካልሆነ ሳይገላበጥ እንደቀረ አሻሮ አሮና ከስሎ ይቀራል፡፡ በዛሬዋ ዓለማችን በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተዳደሩ ሕዝቦች ቁጥራቸው በርካታ ሚሊዮን ነው፡፡ የዴሞክራሲን ትርጉምና ፍች ለመረዳት ቃሉንና ተግባረን ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም ወዳስተዋወቁት ወደ ግሪኮቹ፥ ወደነአርስቶትል መሄድ ለያስፈልገን ይችላል፡፡ ብቻ ከብዙ ዓመተ-ዓለም በፊት ቃሉን ያመጡት የግሪክ ፈላስፋዎች መሆናቸውን ታሪክ መመዝገቡን ግን እንረዳለን፡፡ ዴሞ ማለት ሕዝብ መሆኑንና ክራሲ ማለት ደግሞ ሥርዓት ፥ አስተዳደር ና አገዛዝ እንደሆነ ትርጉሙን ሰጥተው አለፈዋል፡፡ ሁለቱን ቃሎች ገጥመው ደግሞ፥ ዴሞክራሲ ማለት የሕዝብ/ ባዊ ሥርዓት የሚል ሙሉ ፍች ሰጥተው ሄደዋል፡፡ ያም ተባለ ይህ በዘመናችን አማራጫቸውን መርጠው በዴሞክራሲ ሥርዓት ከሚተዳደሩት ሕዝቦች መመልከት እንችላለን፡፡ ይህም ስለተባለ ደግሞ የተያዘ-የተረዘዘው የዴሞክራሲን ነባቢት ስላንምበለበለ ብቻ ዕውነተኛውን የዴሞክራሲ ሥርዓት በሚገባ ተርጉሞ በተግባር አውሎታል ለማለት ይከብዳል፡፡

በነፃነት፥በሥልጣኔና በሃይማኖት ስም በታሪክ ልዩ ግፍና በደሎች በሰዎች ላይ እንደተፈፀሙ ሁሉ ፥ በዴሞክራሲም ስም ተመሳሳይ ወንጀሎች እንደተሰሩ በርካታ የታሪክ መጽሀፍት ያስረዳሉ፡፡በእኛይቱ ሀገርም እንኳን ሳይቀር ለአለፉት አርባ ዓመታት የተፈራረቁት አገዛዞች ለሥርዓቶቻቸው እንዲጠቅማቸው አድርገው የዴሞክራሲን ስም እንዳሻቸው ተጠቅመውበታል ፡፡ ለሕዝቡ አማራጮችን ሳያቀርቡ ለአገዛዛቸው የሚጠቅማቸውን የራሳቸውን የዴሞክራሲ ጥብቆ እየሰፉ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጠባቡ እንዲያጠልቀውና እንዲገዛላቸው አድርገዋል ፡፡ አማራጭ አልባ አድረገው የነሱን ምርጫ ብቻ እንዲመርጥ አላግጠውበታል ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ የውጭ ባዕዳን ፥ በሥልጣኔ ስም ፥ የራሱ ገዥዎች ደግሞ በዴሞክራሲና በሶሻሊዝም ስም የደም እንባ እያስለቀሱ ገዝተውታል፡፡ ክብሩንና ሰብዕናውን

ገፈውታል። ሀብት ንብረቱን ዘርፈውታል። በታሪክ ህግና ሂደት መሠረት ፥  አሮጌው ሥርዓት በህዝብ አመጽ ሲወገድ አዲስ መጭው ደግሞ በተራው ለራሱ የሚያገለግለውን የዲሞክራሲ ለምድ እየሰፋ ያገዛዝ ቀንበሩን በከፋ መልኩ ይዘረጋል። ይህ የማያቋርጥ አሳዛኝ ነባራዊ ሁኔታ፥ የታሪካችን ሂደት ሆኖ ቆይቷል። አሁንም ያለፈውን የመከራ አገዛዝ እያወሱ ከመኖር አልፎ፥ ያለፈው መከራ  እንዳይደገም  ለአዲስ ራዕይና ለብሩኅ ተስፋ የሚሆን አማራጫ ለማቅረብ አልተቻለም ። ለረዥም ራዕይ ፥ ለብሩኅ ተስፋና ለአዲስ አማራጭ የሚሆን ዝግጅት እየተደረገ አይደለም ። ይህ መሆኑ  ቀርቶ  ሁሉም የሚፋጀውና የሚራኮተው ፥ እነመለስን ተክቶ የእነርሱን ጠባብ ብሄረተኛ ሥርዓት በአዲስ ለምድ ሸፍኖ ለመግዛት ነው ።ለሕዝቡም ያለውን ሥርዓት አንግበን መጥተናልና እንደአማራጭ ተቀበልን ሊሉት ይፈልጋሉ። እነስየ አብርሃና ገብሩ አስራት ከነአጃቢዎቻቸውና ተስፈኞቻቸው ጋር አሁን የሚያደርጉት ሙከራ ይህንኑ ነው። እንደገና እናታልልሃለን ፥ ዓይንህን ጨፍንህ ተቀበለን።

ለጊዜው እንኳን ቢሆን፥ የዴሞክራሲን ሰፊና ጥልቅ ትንታኔና ትርጉም ለመስጠት ወደ ሚያስችለው ጉዳና ለመሄድ ተቆጥበን ፥ ለትግላችን ሂደት ሊጠቅመን የሚያስችለውን ተግባራዊ ማስታዎሻ ለመገንዝብ ወደሚያስችለንን ቀላል ትርጉም ስናተኩር፥ ዴሞክራሲ ማለት ልዩነቶችን እያቻቻሉ ማስተናገድ፤በተለየመ የውሁዳንን አቋምንም ማክበር ወደሚል ድምዳሜ ልንደርስ ወደ ምንችልበት ግንዛቤ እናመራለን ። በዕርግጥም ይህንን ግንዛቤ ሁላችንም ከተረዳን ፥ ሌላው ቢቀር ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ተቀዋሚው ጎራ በሚባለው መካከል የተጋረደውን ጥላሸት በመጠኑም ቢሆን ሊገፍፈው ይችላል ብለን እንገምታል ።የዴሞክራሲን ትርጉም በዚህች በቀላል አገላለጽ ለመወስን የተገደድነው ፥ ምናልባት የሀገራቸውን ጥፋት የተረዱ ክፍሎች በባኅርይና በተለያዩ የግለሰቦች ጠባይ ምክንያት የሚፈጠሩትን መሠረታዊ ያልሆኑ ችግሮችን ሊፈቱ ይችሉ የሆናል ከሚል ተስፋ ነው። ሁሉም ባይሆኑ እንኳን የተወሰኑ ክፍሎች በሀገሪቱ አንኳር አንኳር በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ አመለካከትና አቋም እንዳላቸው በአደባባይ ይናገራሉ ። በነባቢት ይገልፃሉ ። ታዲያ ይህ ከሆነ ለምን ለመስማማት እንዳልተቻለ ሲጠየቁ ፥ የሚያቀርቡት ምክንያት ፥ ከነፍሰ-ወከፍ ባኅርይና ከግላዊ ዐመል ያለፈ ሆኖ አይታይም ። ይህም የግል ከንቱ ውዳሴን በቀቢፀ-ተስፋ ላይ የተመሠረተን የሥነ አዕምሮ ችግር፥ የየግል ድርጅትን ጥቅም ማስቀደም ወዘተ ከመሳሰሉት ሊዘል እንደማይችል ለሁሉም ግልፅ ነው ። ይህንን ሁሉ ለመጥቀስ የተገደድነው አማራጭን ለመፈለግ በሚደረገው ጥረት ሊያበረክት የሚችል የአማራጭ ምርጫ ካለ እርሱን እንዳማራጭ መምረጥ ፥ እርሱ ራሱ አማራጭ ሆኖ ሊቀርብ ይችል ይሆን ወይ ? ከሚል ጥያቄ አዘል ጉስጎሳ ለማቅረብ ከሚል ነው።

እኛ የዲሞክራሲ አማራጭ ስንል÷ ሦስት ዐበይት ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ነው ። አንደኛውና ዓይነተኛው÷ ጊዜ የማይሽረውን የሀገራችንንና የሕዝባችንን ስትራተጃዊ ወይም ዘላቂ ጥቅም ከማስጠበቅ ዕምነት ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ ÷ የወቅቱን የሀገራችንን ስር የሰደደ ችግር ከማስወገድ አኳያ ነው ። በሦስተኛ ደረጃ የፓርቲያችንን መሠረታዊና ብሄራዊ ዓላማን አንግቦ ከመታገል አንፃር ሆኖ÷ የወደፊቷን ኢትዮጵያና የዜጎቿን ራዕይና ብሩኅ ተስፋ ከማስተናገድ አኳያ ነው ። እነኝህን መሠረታዊ ጉዳዮች በግምት ውስጥ በማስገባት ነበር ኢሕአፓ በየወቅቱ እንደየ ሁኔታውና አስፈላጊነቱ ÷ ተስማሚ የሆኑ የዲሞክራሲ አማራጮችን ለሕዝብ እያስታወቀ ሲታገል የቆየው ። ሦስቱም ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች እየመጡ በሚጠፉበት አጋጣሚዎች ሁሉ ከአንድ አምባገነን ሥርዓት ወደ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደት መረማመድ ካስፈለገ÷በግድ የሽግግር ወቅትና ሁኔታ የሚያስፈልግ መሆኑን በበቂ ማስረጃና ትንታኔ የተደገፈ ሰነድ አቅርቧል።አሁንም ሀገራችንን ከሚያንዣብብባት ሀገራዊ ቀውስ ለማዳን ÷ በዲሞክራሲያዊ አማራጭ ላይ በተመሠረተ የሽግግር ወቅትን ያካተተ ሰነድ አዘጋጅቶ ለሕዝብ ማቅረብ ወቅታዊና ቀጠይ ተልዕኮው መሆኑን ያምንበታል ።ይህንን የሚገፋውም ወያኔዎቹ ሀገሪቱን አፈረካክሰው በሚጠፉበት ወቅት በሚፈጠረው ቀውስ የሰላምና የብሔራዊ ዕርቅ አማራጭ ለማቅረብ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በሱዳን እንኳን አክራሪ ፖለቲካን በመግፋት ዋና የነበረው ሼክ ሀሰን አልቱራቢ የሽግግር መንግሥስት ተቋቁሞ ከዚያ በኋላ ምርጫ ይካሄድ ሲል እየተደመጠ ነው ። በኢትዮጵያ በሰላምና ዕርቅ አማካይነት የተሻለ አማራጭን ለማቅረብ ኢሕአፓም ሌሎቸም በተደጋጋሚ ሞክረው ያገኙት ምላሽ የወያኔን እምቢታና አልፎም ÷ የነአቶ አበራ የማነአብ የቆየ እስር እንዳሳየው አፈናን ነው ። ከተጫበጭ ተመክሮ በመነሳት ያለውን አመራጭ ስንጠቁም÷ ዛሬ ያለፈውንና አልሰራ ያለውን ጎዳና መከተሉ በራስ ላይ ቀንበርን ማክበድ በመሆኑ÷ የዴሞክራሲ አማራጭን ስናቀርብ ይህ ሂደት የወያኔን አገዛዝ በመገርሰስ ላይ በግድ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ጫና ሰጥተን እናቀርባለን ። ያለውን ዘረኛና አረመኔ አገዛዝ በአስከፊ መልኩ ቁንጮውን ብቻ ከርክሞ ለመቀጠል የሚመኙትና ለፈፀሙብን ወንጅል ይቅርታ ሊጠየቁን እንኳን ያልከጀሉትን መንገድ ልንከተል ከቶም የሚታሰብ ሊሆን አይችልም ። ከወያኔ ጠባችን ከአገዛዙና ከሥርዓቱ ነው እንጂ ለግለሰቡ መለስ ብቻ አለመሆኑ መታወቅ አለበት ። ከዚህ ባሻገር ደግሞ በ1997 የወያኔ የምርጫ ጎዳና ከየት እደ ሚያደርስ የተመለከትነው ነው ። ከ 200 ዜጋ በላይ በጠራራ ፀሀይ ተገድለዋል ። ከሃያ ሺ ያላነሱ ዜጎች ወደ ዴዴሳ ፣ዝዋይ ፣ ብር ሸለቆና ልቱ ልዩ ማጎሪያዎች ተውርውረዋል ። ብዙዎች ተሰደዋል ።በርከታ ዜጎች ከሥራቸውና ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ወያኔ በኃይልና

በዕብሪት ተመልሶ የሥልጣን ባለቤት ሆኖ ፓርላማ ተብዬ አዳራሹን በቅጥረኞችና ሆዳሞች አጃቢነት ሞልቶ ቀልዱንና ግፉን ቀጥሏል። ታዲያ ይህን በሕዝብ ላይ የሚቀልድ ሂደት ዳግም በ 2002 መድገሙ እንዴትስ ሊታሰብ ይችላል? ወያኔና የጡት አባቶቹ ፥ ተቃዋሚ ኃይሎች አመራጭ የላቸውም ቢሉም፥ ኢሕአፓ በበኩሉ ያለውን አማራጭ ደግሞና ደጋግሞ አቅርቧል ። አማራጭ ሲባል ካለው መከራ የሚያወጣ መንገድ ማለት በመሆኑ ፥ በመቸስ ማል ጎደኒ ? ወያኔን ጠረብ ጠረብ አድርጎ በአዲስ መልክ ለማስቀጠል መሞከር ፥ ሕዝብ ሊፈልግ የሚችለው አማራጭ ሊሆን አይችልም። ዛሬ የወያኔ የገማና የገለማ አገዛዝ ሀገሪቷን ለጥፋት ዳርጓልና፥ ይህን የጥፋት ፖለቲካና የዘረኛ መንገድ መሰረዝና ማስወገድ የግድ አስፈላጊ ነው ። የጥገና ለውጥ የሚታዘዝለት በሽታ አይደለም። ቁስል ሲያመረቅዝ እግርና እጅን መቁረጥ ግድ ይሆናል እንደሚባለው ሁሉ የወያኔ ሥርዓት ካልተወገደ የኢትዮጵያ ቁስል አይሽርም ። በምጣድ ማሚሻ ወገብን ማሸት፥ ካመረረ የወገብ በሽታ አያድንም ። የወያኔ አገዛዝ ዘረኝነትን አስፍኖ ዕልቂትን አባብሶ ሀገርን እያጠፋ ያለ ነውና በምህላ፥ ኢትዮጵያን አምርረው የሚጠሉትን እነ መለስና ስብሐትን በመማፀን የሚገኝ መፍትሄ የለም ። ያለን አማራጭ ይህን ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ማውድም ብቻ ነው ። ከዚህ አገዛዝ ጋር ጠቀመን ተጠቀምን ብለው የተሰለፉና የተኮለኮሉ ካሉ ፥ ከወዲሁ ከስህተታቸው ተምረው ከሕዝብ ጎራ ሊደባለቁ ካልሞከሩ፥ የማይቀረው እሳት የሚለበልባቸው መሆኑ አይቀሬ ነው።

አማራጭ ሞልቷል፤ ተጠቁማልም። የዴሞክራሲ አማራጭ ነው። የወያኔ መቸነፍና መወገድ ጠያቂ አማራጭ ነው ። መለስ ባዘጋጀው ምርጫ የመሳተፍ መርጫ አይደለም። መለስን በሌላ ወያኔ የመተካት ምርጫ አይደለም። አለትግል ስርየት የለምና ፀረ ወያኔ ትግልን የግድ የሚል አማራጭ ነው። ሕዝባዊ፤ ኢትዮጵያዊ አማራጭ ! ኢትዮጵያዊ አማራጭ ማቅረብ ደግሞ የአማረጮች ሁሉ አልፋ ኦሜጋ ነው ። የኢሕአፓም አማራጭ ይህ ብቻ ነው !